**‹ቢለያይም ቋንቋው ፣ ደማችን አንድ ነው!›**

የመፅሃፉ ርዕስ ፤ *የኦሮሞ እና የአማራ እውነተኛው የዘር ምንጭ*

ደራሲ ፤ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ

ህትመት ፤ አዲስ አበባ ፣ ኒባዳን አሳታሚ ፣ ሃምሌ 2008 ዓ.ም

የገጽ ብዛት ፤ 275

ዋጋ ፤ 91 ብር

**እንደ መግቢያ**

ስለኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ ፣ ስለ አማራ ማንነት ፣ ስለ ኦሮሞ ህዝብ አመጣጥ በርካታ መፃህፍት ተፅፈዋል፡፡ ኦሮሞና አማራን አብሮ በደግ የሚያነሳ ነገር ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? በበኩሌ በሁለቱ አንጋፋ ብሄረሰቦች ጉዳይ ላይ በቅጡ ያሰበ ደራሲ የማውቀው ተድላ ሃይሌን ነው፡፡ ተድላ በ1922 ዓ.ም የዶክቶራል ጥናታቸው ‹ኢትዮጵያ በዘመናዊነት ወደፊት መራመድ ከፈለገች ኦሮሞና አማራን በማዋሃድ አንድ ህዝብ ማድረግ አለባት› ብለው ነበር፡፡ በዛሬ ዓይን የተድላ ዝርዝር የውህደት መፍትሄ ኋላቀር ወይም ‹ትምክህተኛ› ሊባልም ይችል ይሆናል፡፡ የመነሻ ሃሳቡን እውነታ ግን ፍጹም አያሳንሰውም፡፡ አንድ የማይታበል ሀቅ ቢኖር የዚህች ሀገር እጣ ፈንታ ግንባር ቀደም ወሳኞች ሁለቱ ህዝቦች ናቸው፡፡

የአማራ - ኦሮሞን ግንኙነት ቁምነገር ጠንቅቀው የተረዱት የኢትዮጵያ ታሪካዊና ወቅታዊ ጠላቶች ግን እነዚህን ህዝቦች ለመነጣጠልና ለማጋጨት ባጅተዋል፡፡ ፋሽስት ጣልያንም ፣ እንግሊዝም ፣ ሶማሊያም ፣ የነሱ አንጋቾችና ሀገር በቀል የጎሣ ነጋዴዎችም ያደረጁብን መርዝ ብሄራዊ ህልውናችንን ክፉኛ ተፈታትኖታል፡፡ በተለይ ያ ትውልድ ‹ማነው ኢትዮጵያዊ?› የሚል አመፃ ካነሳበት ጀምሮ ለግማሽ ምዕት የዘለቀው መሰሪነትና አሉባልታ ፣ ኦሮሞና አማራን ከዘልማድ ዘውግ ጠቀስ መቀናቀን ወደ ታሪካዊ ጠላትነት ፣ አልፎም ወደ ቅራኔ አልፋና ኦሜጋነት አድርሷቸዋል፡፡ በውጤቱም ሚሊዮኖች ህይወት ፣ አካልና ንብረት ከፍለውበታል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ንኡሳን ብልጣብልጦች የማያልቅ ትርፍ ሲዝቁበት ኖረዋል፡፡

ሰሞኑን ለንባብ የበቃው የፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ *የኦሮሞ እና የአማራ እውነተኛ የዘር ምንጭ* መፅሃፍ ይህን የተቃርኖ አውድ የገሠሠ ፣ ታሪካችንን የምንረዳበትን መንፈስ የከለሰ ስራ ነው፡፡ ከልዩነታችን ይልቅ በእድሜ ጠገቡ ቋጠሯችን ላይ ያተኩራል፡፡ ምንጮቹን ከሥነ ፅሁፍ ፣ ባህልና ፍልስፍና ጓዳችን ይቀዳል፡፡ ብሄራዊ ራስ ምታት የሆኑብንን አንኳር ጉዳዮች እያነሳና እያጠየቀ ፣ ‹አዲስ ታሪክ› ያቀርብልናል (8)፡፡ እንግዳ ጭብጡ ፣ የትረካው ይዘትና አዎንታዊ መልእክት ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር ተደማምሮ አነጋጋሪ ስላደረገው ስለዚህ መፅሃፍ በበኩሌ የታየኝን ሃሳብ እነሆ ብያለሁ፡፡

**እውን አዳም ጎጃሜ ነውን ?**

‹የሰው ልጅ ታሪክ እንጂ ተፈጥሮ የለውም› ይላል እስፓኛዊው ሊቅ ኦርቴጋ ኢ ጋሴት፡፡ *የኦሮምና አማራ ዘር መፅሃፍ* እንደታተመ በማህበራዊ ድረ-ገፅ የናኘው ‹አዳም ጎጃሜው ነው› አሉባልታ ፣ ይህን ማንነትን ከታሪክ የሚያቆራኝ ፍልስፍናውንና ትኩረቱን እንደዋዛ ይጠቁማል፡፡ የፍቅሬ መፅሃፍ ‹ኦሮሞ› ፣ ‹አማራ› ፣ ‹ኢትዮጵያ› በሚሉ ዋና ዘውጎች ላይ ተመስርቶ ብሄራዊ አሻራችንን አሪታዊው ጭጋግ ውስጥ የሚፈልግ ሲሆን ፣ በተለይም ከሁለቱ ህዝቦች ከ3500 ዓመታት የዘለቀ መስተጋብር አንጻር በሚተነትኑ ሶስት አበይት ክፍሎች ተዋቅሯል፡፡ ፍሬ ሃሳባቸውን ባጭር ባጭር እንመልከት፡፡

ክፍል አንድ (15–36) ኦሮሞ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያበረከተውን ሥነ-ልሳናዊ ፣ ፍልስፍናዊ ፣ መንፈሳዊ ፣ ወታደራዊ ፣ ትምህርታዊ ፣ ሥነ-ቃላዊ ፣ ሥነ-ጥበባዊ እንዲሁም ሌሎችንም ተዛማጅ አስተዋጽኦዎች ያብራራል፡፡ እግረ መንገዱንም ኦሮሞና አማራ በዘመነ ዘመናት ዝምድና የተለዋወጧቸውን ፈርጀ ብዙ እሴቶች በማሳየት ፣ እነዚህን የህዝቦች አንድነት ድርና ማጎች ፈልጎ የማጥናትን ጠቃሚነትን ያስገነዝባል (34)፡፡

የመፅሃፉ አስኳል የሆነው ክፍል ሁለት (37–144) ስለኦሮሞና አማራ የዘር ግንድ ምንነትና አነሳስ ፣ ስለኢትዮጵያዊ እትብታቸው ዝንታዊነትና ጥብቀት ፣ አስገራሚ ትርክቶችን ይዟል፡፡ አማሮችም ሆነ ኦሮሞዎች መጤም ፣ ወራሪም ፣ ጠላቶችም ሳይሆኑ ፣ ከኢትዮጵያ እምብርት ከጎጃም የመነጬ ወንድማማች ህዝቦች ናቸው፡፡ በዚህ ላይ የኢትዮጵያ መሥራች የሆነው የኢትዮጵ ልጅ ደሴት ወይም ደሸት ‹የኦሮሞ አባትና የአማራ አያት› መሆኑ ፣ በዘር ሁለቱንም ኩሻውያን ያደርጋቸዋል ይለናል(10-11 ፣ 52-55 ፣ 68)፡፡ እንግዲህ አዳም ጎጃሜ ሆነም አልሆነ ፣ የኢትዮጵያውያን ጎጃሜነት አያጠራጥርም ማለት ይመስለኛል፡፡

ክፍል ሶስት ደግሞ (145–271) በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የአማራውን ሚና በማተት ፣ ከዚያ አንጻር በብሄራዊ ህይወታችን ውስጥ ሥር የሰደዱ ይትበሃሎችን ፣ ቅሬታዎችንና ጥያቄዎችን ፋይዳ ይገመግማል፡፡ ታሪክን ስንመረምር አማራው በስሙ የመሰረተው ሥርወ መንግሥት አልነበረም (193)፡፡ እንዲያውም ባለፉት 700 ዓመታት በሰለሞናዊው አልጋ ተቀምጦ የገዛው ከአማራው ይልቅ ኦሮሞው ነው ይለናል (189 ፣ 191)፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ አማራው እስካሁን በገዥና በጨቋኝ ስም ለጥቃት የሚጋለጥበት ምክንያቶች ፣ ቋንቋው የመንግሥት አፍ መሆኑ ፣ ስሙ ከክርስቲያንነት መሳነቱ ፣ ታሪካዊው ሀቅ በቅጡ አለመታወቁ ፣ በተለይም ደግሞ ለፖለቲካ ትርፍ ሲባል እንደ ‹ማታገያ ጠላት› መፈረጁ ናቸው (237 ፣ 243–44)፡፡

በአጠቃላይ መፅሃፉ አዳዲስ እማኞችን ፣ ያልተሰሙ ታሪኮችን ፣ ሥር ነቀል አንድምታዎችን ያካተተ ቢሆንም፣ የየክፍሉን ማዕከላዊ ሃሳቦች ልብ እናድርግ፡፡ አንደኛ በሀገራችን ያንድ ወገን ብቻ ባህላዊ ተፅእኖ አልነበረም፡፡ ሁለተኛ ኦሮሞና አማራ ጥንታዊ ወንድማማቾች ናቸው፡፡ ሶስተኛ አማራው እንደሚባልለት የተጋነነ የፖለቲካ ሥልጣን አልነበረውም፡፡ እነዚህ ባህልን ከዘርና ከፖለቲካ ታሪክ በሰፊው በማጣቀስ የነጠሩ ጭብጦች ፣ በፍትህና እኩልነት ስም በብሄራዊ ማንነታችንና ታሪካችን ዙሪያ የተቀነቀኑ ውዥንብሮችንና ፅንፈኛ አተካሮዎችን መሰረት የሚንዱባቸው ናቸው፡፡

**ወደኋላ ዞሮ ወደፊት የሚያየው ታሪክ !**

‹ታሪክ የሚጠናው ለዛሬና ለነገ እንጂ ለትናንት አይደለም› የሚል ነባር ብሂል አለ፡፡ ዞሮ የማየት ፋይዳው ከውድቀታችን በመማርና ከስኬታችን በማትረፍ ፣ የተሻለች ዓለም እንድንሰራበት ነው፡፡ ይህ ታላቅ ሃላፊነት ሀቀኝነትን ፣ ሚዛናዊነትን ፣ አርቆ ተመልካችነትና የዚህ ሁሉ መቋጠሪያውን አዎንታዊነት ይጠይቃል፡፡ *የኦሮሞና አማራ ዘር* መፅሃፍ ዋነኛ መለያው እነዚህን በታሪክ አያያዛችን ብርቅ የሆኑብንን በጎ ባህርያት አቅም በፈቀደ መላበሱ ነው፡፡

ታሪክን ለገንቢ ዓላማ የማዋል አንገብጋቢነት ፣ ከተጨባጭ ስጋትና የመፍትሄው ጥያቄ ይነሳል፡፡ ከሀገራችን ጥንታዊነት ፣ ነፃነትና ክብር አንፃር ፣ ከፉኛ የሚንጠን ብሄራዊ ውዥንብር ፣ ውርደትና የህልውና አደጋ ያባንናል፡፡ መፅሃፉ የዚህ ምፀታዊ ፍዳ ጦስ የሆኑትን ድንቁርናንና ሽፍጥን ፣ በእውቀትና በቅንነት በመቃወም ማህበራዊ ሰላም ፣ ህብርና ልዕልና እናገኛለን የሚል ይመስላል፡፡ ስለዚህም የማንነታችንን እንቆቅልሾች እየፈታ በራስ መተማመን ፣ ብርሃንና ተስፋ የሚፈነጥቁ ሶስት አንኳር መልእክቶችን ያቀርብልናል፡፡

የመጀመሪያው ብሄራዊ አንድነት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነታችን በደም ፣ በባህልና በታሪክ የታተመና በሀገር በቀል ትዕምርታዊ ቅርሶች የሚገለጥ መሆኑን ለማረጋገጥ ይሞክራል፡፡ ጥንታዊው የጋራ ቋንቋችን ሳባ ሳይሆን ሱባ ነው፡፡ ስሞቻችን ኢትዮጵ/ያ (ለእግዚአብሄር የቢጫ ወርቅ ስጦታ) ፣ ኦሮሞ (እውቀት ገላጭ ፣ ተርጓሚ ፣ ብልህ ሰው) ፣ አማራ (እውነተኛ ብርሃን) ከዚሁ የፈለቁ ናቸው (62 ፣ 76)፡፡ በእርግጥ ሰንደቅ ዓላማችን ቀስተ ደመናዊ የቃልኪዳን ተምሳሌት ናት፡፡ ሆኖም ፈጣሪዋ ቀዳማዊም ዳግማዊም ሚኒልክ ሳይሆኑ ፣ በንግሥ ስሙ ‹ሰንደቅ አልማ› ይባል የነበረው እሴ ወይም አጼ ከ3400 ዓመት በፊት ነው (129)፡፡

ሁለተኛው ብሄራዊ እኩልነት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታችን አመሳሶ የለውም፡፡ በኩርም ባይተዋርም የለብንም፡፡ የሀገራችንን በረከቷንም ፍዳዋንም በጋራ ተቋድሰናል፡፡ በየፊናችንም አሻራችንን አኑረናል፡፡ ስለዚህ ቅርሷም ፣ ክብሯም ፣ እጣ ፈንታዋም የሁላችን እንጂ ‹ያንድ ነገድ የግል ንብረት አይደሉም› (102)፡፡ ይህን ከተረዳን ዘንዳ ፣ የራሳችንን ጥለን የባእድ መቀላወጥ አይገባንም (99)፡፡

ሶስተኛው ብሄራዊ ኩራት ነው፡፡ ኢትዮጵያችን ከማንም ከምንም በላይ ናት፡፡ የሰው ዘር ፣ ቋንቋ ፣ እምነት ፣ ሥልጣኔ ምንጭ ናት (93-97)፡፡ ከኖህ እስከ ሙሴ ፣ ከኤልያስና ከእዮብ እስከ ክርስቶስ ያከበሯት ቅድስት ምድር ናት፡፡ ኢትዮጵያውያን ምርጥ ህዝቦች ነን፡፡ በጀግንነት የሚስተካከለን የለም፡፡ ክርስትናን የተቀበልነው ከማንም በፊት ነው (184)፡፡ አለም ፊደላቱን የኮረጀውም ከኛ ነው (98)፡፡ ታዲያ በኢትዮጵያዊነት ያልኮራን በምን ልንኮራ ነው?

እንግዲህ ዘረኝነት የማይነካካው የዘር ሃተታ ማለት ይህ ነው፡፡ የመፅሃፉ ርዕስና ርዕሰ ጉዳይ የማይሰምርልን ፣ በተለይ ከኦሮሞና አማራ ረገድ ያቀረቡት ሰፊ ትንታኔ ፣ ዞሮዞሮ ብሄራዊ ዒላማቸውን የሚያጠናክር ንዑስ ጭብጥ መሆኑን ስናስተውል ነው፡፡ በዚህ ረገድ የየክፍሉ ማዕከላዊ ሃሳቦች ብለን ከላይ ምልክት ያኖርንባቸው ባህል ፣ ዘርና ፖለቲካ ጠቀስ ድምዳሜዎች ላይ ተመርኩዞ ፣ እስከዛሬ በዘውግ ፖለቲካችን ያራመድናቸው አቋሞች ሚዛን የጎደላቸው ፣ ፈጠራና አሉታዊነት የገነነባቸው መሆናቸውን ይተቻል፡፡

ታሪክን ከጠባብ ፍላጎታችን ደንገጡርነት በላቀ ብሄራዊ መንፈስ ፣ በአዎንታዊነትና በሀቅ ካየነው ፣ ‹አማራ የኦሮሞ ረዳቱ እንጂ ጠላቱ አልነበረም› (121)፡፡ አብዛኞቹ ጎሰኛ ምሬቶቻችንንም አለቅጥ የተጋነኑ ወይም ከናካቴው በምናባዊ በደሎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ለአብነት አማራው ባህሉንና ቋንቋውን በሃይልም ሆነ በህግ አስገድዶ ለመጫን ሥልጣኑም ተፈጥሮአዊ ባህርዩም አልነበረውም፡፡ ራሱም በሩን ከፍቶ ስለኖረ ተጽእኖው ሁለትዮሽ ፣ በገዛ ፈቃዳችንና በተፈጥሮአዊ መንገድ የተከናወነ ነው እያለ ይሞግተናል (110 ፣ 111)፡፡ በአጠቃላይ አይኑን ከብሄራዊ ትኩረቱ ሳይነቅል ፣ ለሀገራችንም ሆነ በተለይ ለአማራና ኦሮሞው የሚበጀው ፣ ሆደ ሰፊነት ፣ መተማመንና ታሪካዊ ሀቅን ከጋራ ጥቅሞቻችን ጋር አቻችለን ለማሰብ መዘጋጀት ነው ሲል ይደመድማል (103 -4 ፣ 230)፡፡

## ማጠቃለያ

ደራሲው እንዲህ በየገጹ የሚንተገተገው ኢትዮጵያዊነታቸውና በዘመኑ ዓይን ‹መናፍቃዊ› የሚሰኙ አመለካከቶቻቸው ፣ ከተለያየ ፅንፍ ኡኡታ እንደሚያስነሳባቸው እገምታለሁ፡፡ የሚገርም ቢሆንም ዋናው መወቀሻቸው ቅንነታቸውና አዎንታዊነታቸው የሚሆንም ይመስለኛል፡፡ ዛሬ ስለጋራ ማንነታችንና ህብረ ታሪካችን ማንሳት ከማስከሰስና ማስወቀስ አልፎም ከነፈዝ ማስቆጠር መድረሱን ሁላችንም እናውቃለንና፡፡

ጠንካራው ብሄራዊ ስብዕናቸው ፣ ከተለመደው የጎሳ እግረሙቅ መላቀቃቸውና ሁለቱ ጉዳዮች ተፃራሪ ሳይሆኑ ተደጋጋፊ የማንነታችን አካላት መሆናቸውን ማሳየታቸው የሚደነቅ ነው፡፡ ይህ ከደመነፍሳዊነት የላቀ የመመልከቻ ማማቸው ለድርሰታቸው ሚዛናዊነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡ እግረ መንገዳቸውንም ዋናው በሽታችን በመካከላችን የጎሳ ግንቦች ገንብተን እርስ በርስ ለመተያየትና ለመደማመጥ አለመቻላችን መሆኑን አግኝተውልናል፡፡

ከባህላዊው የቤተክህነት ታሪክ አጻጻፍ የሚመሳሰል ፣ ለትውፊታዊና መለኮታዊ ትርክቶችና ትርጓሜዎች ሁነኛ ሥፍራ የሚሰጥ አካሄድ መምረጣቸው ጥቂት ቅንድብ ሊያስቋጥርባቸው ይችል ይሆናል፡፡ እንደሚሰማኝ ምክንያቱ ሀገራዊ ብሄርተኝነታቸው ፣ ምሁራዊ ዝንባሌያቸው ፣ ብሎም ዋነኛ ምንጮቻቸው ሃይማኖታዊ ባህሪ ያላቸው ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሰነዶችና መጽሃፍ ቅዱስ ጭምር የመሆናቸው ድምር ነው፡፡ እውነትን ማንጠሪያቸውን መወሰን ድርሻቸው ነውና ፣ ይህንን ወይም ያንን ዘይቤ ተከተሉ ብለን ልንወቅሳቸው አንችልም፡፡

በበኩሌ አሳሳቢ የሚመስለኝ አመዛኙ የድርሰታቸው መሰረት የመሪራስ አማን ትርጉሞች መሆናቸው ፣ በመረጃቸው ወርድና ተአማኒነት ላይ ሊያሳድር የሚችለው ውሱንነት ነው፡፡ በዚህ ላይ ገና ሰነዶቹ ቁም ነገራቸው በቅጡ አልተመረመረም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ፍቅሬ እንዴት ሙሉ እምነት እንደጣሉባቸው ስለማይነግሩን ጥርጣሬያችን አይቀርም፡፡ ለምሳሌ የመፅሃፈ ሱባኤ ዋናው ዘር በዘመነ አክሱም መደረሱን ብንቀበልና ፣ የጀበል ኑባው ቅጅ የዘመነ ኢያሱ አዲያም ሰገድ ከሆነ (10 ፣ 93) ፣ በሁለቱ መካከል ስላለው ወርጅናሌነት እንዴት እርግጠኛ መሆን ይቻላል?

በሌላ በኩል በተለይ በቃላት ድምጸትና ትርጉም ተመሳሳይነት ፣ ለምሳሌ ፖርት-ጋል ፣ ሰጺራ ፣ ኦፊር ፣ እነማይ ፣ ወዘተ ፣ አማካይነት የሚያቀርቡት ማረጋገጫ አከራካሪ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ ያሉ ድሮና ዘንድሮን የተንተራሱ የቦታ ፣ የህዝብና የነገር ስሞች ተመሳስሎ እጅግ አሳሳችና ጥንቃቄ የሚሹ መሆኑ ፕሮፌሰር አይሳታቸውም፡፡ አንዳንድ ጊዜም የትውፊቶችን

ትእምርታዊ ዋጋ ከመፈልቀቅ ይልቅ ፣ በጥሬው ከታሪካዊ እውነታዎች እንደመነጩ የመውሰድ አዝማሚያ (euhemerism) የሚታይባቸውም ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ ‹ኦሮሞ ውሃን የሚያፈቅረው ጥንት አባቱ ደሸት በውሃ ውስጥ ስለተጸነሰ ነው ይሉናል›፡፡ ታዲያ ወንድሙ አማራውስ?

እንደገናም ‹ብሄር ጎሳን አይተካም ፣ ቦታን ነው የሚያመለክተው› (70-71) ፣ ‹ብሄር የሚለው ቃል ሀገር ከሚለው ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ አካባቢን ያመለክታል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ አይነቷን ሰፊና ትልቅ ሀገር መግለጽ አይችልም›(72) የሚለውም ስህተት ነው፡፡ እንዲያውም ብሄር በተለዋዋጭ ከትልቁ ዓለማችን እስከ ትንሿ ጎጥ ድረስ የሚወክል ፣ በተለይ ደግሞ ሀገር ፣ መንግሥት ፣ ህዝብ የሚሉትን ትርጉሞች የሚያጠቃልልና ከግሪኩ (*natio*) ወይም ከእንግሊዝኛው (nation) ጋር መሳ የሆነ ቃል ነው፡፡ ብሄረ ኢትዮጵያም ፣ ዘብሄረ አማራም ፣ ዘብሄረ ድሬም ቢሉ ያስኬዳል (ኪዳነወልድ ክፍሌ 1948)፡፡

ምንም ይሁን ምን ግን ደራሲው ታሪካችንን የምንመለከትበት አዲስ ፈርና ቀና መንፈስ አሳይተውናል፡፡ ገና ብዙ የሚያወያይ ታላቅ አጀንዳ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ግሩም መፅሃፍ ፣ እንደ ፍቅሬ በራሱ የሚተማመን ፣ ብሄሩና ጎሳው ጣውንት ያልሆኑበትና ከእውቀትም በላይ እምነት ፣ ፍቅርና ሰብአዊነት የተላበሰ ስብዕና ይጠይቃል፡፡ በዋናነት በውኸ'ንብር ተወናብዶ የመሪ ያለህ ለሚለው ወጣት ትውልድ ብሩህ አድማስ ያሳያል ብዬ አምናለሁ፡፡ በጎጠኝነት እብሪትም ሆነ የበታችነት ደዌ ለሚማቅቁ ደግሞ በግዴታ የሚወሰድ ነው፡፡ በተለይ ኦሮሞና አማራ ደማቸውን በጋራ እያፈሰሱ ባሉበት ፣ ከአንጋፋነታቸውና አቅማቸው የማይሰናኘውን የድክመታቸውና የጥቃታቸውን ጦስ ከተገነዘቡበት ታሪካዊ ወቅት መግጠሙም ድንቅ ነው፡፡ ‹ኦሮሞ ፣ አማራና ኢትዮጵያዊነት› ጊዜው የደረሰ ሃሳብ ነው!

ቴዎድሮሥ ኃይለማርያም (ዶ/ር)